Amen Ethiopia

# የተስፋ ንግደት

## ወደ አዲስ ምዕራፍ

## Pilgrimage of Hope
## Towards a New Chapter



September 2007 - መስከረም ፪ሺ.ህ (2000)

### በሁለት ሺ. ዓመተ ምሕረት - የሦስተኛው ሚሌንየም መግቢያ

# አሜን ኢትዮጵያ

### የተስፋ ንግደት ወደ አዲስ ምዕራፍ

**ዓላማ**

በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የሁለት ሺ.ህ ዓመተ ምሕረትን መግቢያ ምክንያት በማድረግ በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አገር ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር የተስፋ፣ የሰላምና የለውጥ መሻት እንቅስቃሴ ለማካሄድ መርሐ ግብር ነድፈዋል።

የአሜን ኢትዮጵያ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያውያን መካከል ኅብረትንና ብሔራዊ መግባባትን ለማበረታታትና ሕዳሴ-ኢትዮጵያ ሁኖ ሁሉም በመደማመጥና በመግባባት፥ በመቀባበልና በመከባበር፥ በመተሳሰብና በመደጋገፍ ለሀገር እድገትና ብልፅግና በጋራ እንዲሠሩ ጥሪ ለማድረግ ነው።

የአሜን ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ አነሣሽና አስተባባሪ በሆላንድ አገር የሚገኘው አድማስ የተሰኘው በዳች ህግና ደንብ መሰረት የተቋቋመ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነው። የአድማስ ዓላማ ከሃይማኖት ፣ ከዘር ፣ ከጾታ ልዩነትና ከፖለቲካ አመለካከት ወገናዊነት ነጻ በመሆንና በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል እንደ ድልድይ በመሆን፥ ለአገር እድገትና ብልፅግና በኅብረት መሥራትን ማበረታታት ነው።

**የአሜን ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ መነሻ ሃሳብ**

ኢትዮጵያ በሦስተኛው ሚሌኒየም መግቢያ ላይ በተለያየ መልኩ መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። ወቅቱ አገራችን ካለፉት ችግሮችና ስህተቶች ተምራ መልካም በሆነው ታሪካዊ ቅርሷ ላይ በመገንባት የወደፊትዋ ብሩህ እንዲሆን ጥሩ መሠረት እንደትጥል መልካም አጋጣሚ ነው። በተለይ አሁን የዓለማችን የሰላም ሁኔታ በተናጋበት ወቅት ስለ ሰላም ድምፅን ማሰማት አስፈላጊ ነው። ሰላም በመደማመጥና በመግባባት ብሎም በመከባበር በእርቅ ላይ ነው የሚመሠረተው። እርቅ ደግሞ ከራስ ነው የሚጀምረው። ይህ የአዲስ ምዕራፍ ንግደት በኢትዮጵያ የመግባባትንና የእርቅን መንገድ ከዘረጋ ለአፍሪካ ቀንድ ችግርም መፍትሔ ፈር ሊቀድ ይችላል።

የታሪክ ማሕደር እንደሚያስረዳው ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት የተለያዩ የታሪክ፤ የባህልና የእምነት ገፅታዎች ያላት አገር ናት። ታሪካችን በብዙ መልኩ የተወሳሰበና ባህላዊ ገፅታዎቻችንም የተለያዩ በመሆናቸው “ሰላማዊ ሥርዓት” ለመዘርጋት የነበራቸውንና ያላቸውን አስተዋፅዖ ማጤን ይኖርብናል። የአመለካከትና የሃሳብ ልዩነት መኖር ለማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጥሩ መሰረት ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ፡ በልዩነት ላይ የተመሠረተ ኅብረት እንዲዳብር የሚያበረታታ አዲስ ምዕራፍ ይከፈት ዘንድ አሜን ኢትዮጵያ ይህንን እንቅስቃሴ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

በአሜን ኢትዮጵያ አማካኝነት፡ በዓላማ ደረጃ የተያዙትን ነጥቦች ሁሉ በአንድ ጊዜ ከግብ ለማድረስ የሚቻል ባይሆንም ነገር ግን ይህንን ክቡር ዓላማ በዘላቂነት ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም በኅብረት እንዲሰለፍ ጥሪ እናደርጋለን።

## ዐውደ ጥናቶችና ውይይቶች

ለተስፋ ንግደቱ ቅድመ ዝግጅት በአምስተርዳም፣ በለንደን፣ በዋሽግተን ዲሲ፣ በብራስልስ፣ በፍራንክፈርትና በጄኔቭ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎችም አካባቢዎች በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙርያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶችና ሴሚናሮች የሚካሄዱ ሲሆን በተጨማሪም በሐምሌ (ጁላይ) ወር መጨረሻ ላይ በጉዞው መክፈቻ በሆላንድ (ዘሄግ) እና በጉዞው መዝጊያ ኢትዮጵያ (አዲስ አበባ) ታዋቂ ምሁራን፣ የአገር ሽማግሌዎችና ታላላቅ የክብር እንግዶች በተገኙበት ዐውደ ጥናቶች ይካሄዳሉ።

በአዲሱ ዘመን ከታሪካችንም ሆነ አሁን ካለንበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር መልካሙን አጎልብተን፣ ጎጂውንና ደካማውን ጥለን ችግሮቻችን በሰላማዊ መንገድ ለማስወገድ የምንችልበትን ዘዴ ለመጠቀም ከታሪክ ጋር የሚኖረንን ትስስር በመመርመር ሰላምና እርቅን እውን ስለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባዎች፣ ዐውደ-ጥናቶች፣ ማኅበራዊ ውይይቶችና መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ታቅደዋል። በእነዚህም ተግባራት ምሁራንን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ የሙያ ማኅበራትን፣ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን፣ የስፓርት ቤተሰቦችንና ሊሎችንም ለማሳተፍ ጥረት ይደረጋል።

ዛሬ በአገር ደረጃ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ተቋማት ተቀራርበው በመነጋገርና በመግባባት ልዩነታቸውን በመፍታት ሁሉም ለአገራችን የወደፊት ሂደት በተናጠልና በጋራ ለሰላምና ለብልጽግና እንዲሠሩ ጥረት መደረግ አለበት። በዚህ ረገድ በሁሉም ብኄረሰቦችና የሃይማኖት ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ያለው የሽምግልና ባሕላችን በሦስተኛው ሚሌንየም ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።



በተጨማሪም በሁሉም ደረጃ በሚገኘው ኅብረተ-ሰባችን መካከል የግልና የቡድን ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ፤ ሁሉም ኃላፊነት ተሰምቶት ችግሮችን በውይይት የመፍታትና፣ ለአገር ደህንነትና ለጋራ ጥቅም ተከባብሮ በተናጥልና በኅብረት የሚሠራበት ዘመን ይሆን ዘንድ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ገንቢ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉበትን ዘዴ ለመቀየስ ነው።

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሃይማኖት ተቋማት መካከል ትብብር እንዲጨምርና፣ በንግግርና በውይይት ለአገራችን አንገብጋቢ ችግሮች በተለይም ድህነት፣ ተደጋጋሚ ድርቅና ረሃብ፣ የኤድስ በአሳሳቢ ፍጥነት መሰራጨት፣ እንዲሁም ለሌሎች የኅብረተሰቡን ኅልውና ለሚያናጉ ማኅበራዊ ቀውሶች መሠረታዊ መፍትሄ ማምጣት ይቻል ዘንድ የውይይት ብሎም የጋራ ሥራ መድረኮችን ለመፍጠር ነው። በተጨማሪም በህኅብረተሰባችን መካከል በመቀባበል አብሮ የመኖርን አስፈላጊነት በማስጨበጥ ኢትዮጵያውያን ቀጣይነትና ዘለቄታነት ያላቸውን መሰል መርሃ ግብሮች እንዲነድፉና እንዲያስፈጽሙ ለማበረታታት ነው።

በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ አዎንታዊና ገንቢ በሆነ መልክ መሳተፍና አስተዋፅኦ ማበርከት እንዲችሉ፣ እንዲሁም አገር ውስጥ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ለማጥበብ የውይይት መድረኮችን በመክፈት ሁሉም የበኩሉን እንዲያበረክት አሜን ኢትዮጵያ ጥሪ ያቀርባል፣ የበኩሉንም አስተዋፅዖ ያደርጋል።

## መንፈሳዊ መርሐ ግብሮች

ኢትዮጵያውያን ለእምነታቸው ትልቅ አክብሮት ያላቸው በመሆናቸው የሃይማኖት መሪዎች፤ ተከታዮቻቸው በግብረገብ ታንፀው፤ ከሌላው ጋር በሰላም፣ በመቀባበል፣ በመከባበር አብሮ የመኖር ባህልን እንዲያዳብሩ ማስተማር መንፈሳዊ ኃላፊነታቸው መሆኑ ግልጽ።

በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙሪያ በአብያተ ክርስትያናትና በመስጊዶች ተባባሪነት የጸሎት፡ የትምህርት፡ የውይይትና የተለያዩ መንፈሳዊ ዝግቶችን በማድረግ በዓላማ ደረጃ የተያዙት መልእክቶች ለኅብረተ-ሰቡ የሚደርሱባቸውን ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ከሃይማኖት መሪዎች ጋር በመመካከርና ሃሳብ በመቀበል ለመሥራት ታቅዷል።

በሃይማኖት ተቋማት መካካል ተከታታይና ዘላቂ ውይይቶችን ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በመምከር በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች እየተከሰተ ያለው

በታሪካችን ያልተለመደውን የሃይማኖት ግጭት መፍትሔ እንዲያገኝ የጋራ መድረኮችን ማዘጋጀት ይቻል ዘንድ አሜን ኢትዮጵያ ጥረት ያደርጋል።

የአሜን ኢትዮጵያን ዓላማ የሚደግፉ ሁሉ በአዲሱ ሚሌንየም ለኢትዮጵያ ያላቸውን መልካም ምኞትና ጸሎት በመግለጽ የክብር ፊርማቸውን የሚያሰፍሩባቸው መዝገቦች ተዘጋጅተዋል። የተሰፋ ተጓዦችም እነዚህን መልካም ምኞትና የፀሎት ሀሳብ የሰፈረባቸውን የክብር መዝገቦች ይዘው ይጓዛሉ።

## የአሜን ኢትዮጵያ የተስፋ ጉዞ

የአሜን ኢትዮጵያ የተስፋ ጉዞ የሚያደርጉ ነጋድያን ከተለያዩ አገሮች (ከሰሜን አሜሪካ፣ ኤውሮፓ፣ ወዘተ) የተውጣጡ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ከላይ የተጠቀሱትን የአሜን ኢትዮጵያ ዓላማዎች መሠረት በማድረግ፡ ዋና የመነሻ ቦታቸውን በሆላንድ አገር በሄግ ከተማ የሚገኘውን ቤተ ሰላም (Peace Palace) በማድረግ በሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ (July 29) ወደ ብራስልስ በማቅናት፡ ፍራንክፈርት፡ ጀኔቭ፡ ሮም፡ አቴንስ፡ ከዚያም በኢስታንቡል በኩል መከካለኛው ምስራቅን አቋርጠው ወደ ግብፅ ካመሩ በኋላ በሱዳን አድርገው አዲስ ዓመት ከመግባቱ በፊት ኢትዮጵያ ይገባሉ።

በጉዞ ወቅት ከመልክዓ ምድራዊም ሆነ ወቅታዊ ሁኔታዎች አንጻር አንዳንድ አካባቢዎች አስጊነታቸውና መስዋዕትነትን የሚጠይቁ መሆናቸው ቢታወቅም፡ ተጓዦቹ ይዘው የተነሱትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፡ ከፊት ለፊታቸው የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች ሁሉ በትዕግሰት ለመቀበል ራሳቸውን አዘጋጅተዋል። ተጓዦቹ የየራሳቸው የሆነ እምነት፡ ባህላዊ አመለካከት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን በሃይማኖት፣ በባሕልና-ወግ ትስስር ዙሪያ በጉዞው ወቅት የሐሳብ ልውውጥ ያደርጋሉ።

ይህ የተስፋ ጉዞው የራሳችንን ቁስል ዳስን የሌላውንም ቁስልና ብፅዕናውንም ጭምር የምናይበት ዘላቂ የሆነ እንቅስቃሴ ሲሆን ከራሳችን የጠፋውንና የተረሳውን ክፍል ፈልጎ ለማግኘት በውስጣችን የምናደርገው የሀሳብ ጉዞ ጭምር ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ በሦስተኛው ሚሌኒየም ወደ ራሷ የምታደርገውን የአዲስ ምዕራፍ ረጅም ጉዞ ያመልክታል።

በጉዞው ሂደት ላይ በዓለም አቀፍና በኢትዮጵያ ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦች ከተስፋ ተጓዦች ጋር እንደ ፈቃዳቸው የተወሰነ መንገድ አብረው በመጓዝና በሚካሄዱት ተግባራት ላይ በመሳተፍ ድጋፋቸውን ይገልጻሉ።

## በጉዞው ሂደት ላይ የሚከናወኑ ተግባራት



የአሜን ኢትዮጵያ የተስፋ ተጓዦች በሚያልፉባቸው ቦታዎች ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር በመገናኘት ከታሪካችን መልካሙን አዳብረን ጉጂውን ጥለን በጋራና በግል ለአገር ብልፅግና ለባሕል ትስስር ብሎም ለእርቅና ሰላም ስለመሥራት ውውይት ያደርጋሉ።

አገራችን ያሏትን በረዥም ጊዜ የተካበቱ መልካም ገጽታዎቿን በደረሱበት ሁሉ ከፍ አድርጎ በማሳየት ለዓለም ኅብረተሰብ ያስተዋውቃሉ።

በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሃይማኖት ተቋማት መካከል በኅብረት መሥራትን ለማበረታት የአሜን ኢትዮጵያ ተጓዦች በክርስትናና በእስልምና የሃይማኖት ታሪክ ትልቅ ቦታ ባላቸው ከተሞች በኩል በማለፍ በቦታው ከሚገኙ የሃይማኖት መሪዎች ጋር የሐሳብ ልውውጥ ያደርጋሉ።

በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ መርሐ ግብር ውስጥ የኢትዮጵያ ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጠው የተስፋ ተጓዦች በሚያልፉባቸው አገሮች ውስጥ እንደ ሁኔታውና እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙሪያ ውይይት ያደርጋሉ። በጉዞው ዓላማ ዙሪያም በኢትዮጵያ ውስጥ ቀጣይነት ያላቸው ተግባራት ለማከናወን ትብብር ያገኙ ዘንድ ከተለያዩ ልምድ ካላቸው ተቋማት ጋር ምክክር ያደርጋሉ።

በተጨማሪም ከ70 ዓመት በፊት አገራችን ኢትዮጵያ በግፍ በተወረረችበት ወቅት ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ድምጽዋን ማሰማቷን በማስታወስ የአሜን ኢትዮጵያ የተስፋ ተጓዦች በጄኔቫ የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት የመታሰብያ ጉብኝት ያደርጋሉ።

## ተግባራዊ ተሳትፎ

አሜን ኢትዮጵያ የነደፋቸው መርሐ ግብሮች ተፈጻሚነት ይኖራቸው ዘንድ የአገር ጉዳይ የሚገደው ኢትዮጵያዊ ሁሉ መልካም ያልሆነውን ታሪክና የትውልድ አመለካከት ለመቀየር አቅሙ በፈቀደ መጠን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ይጠበቅበታል።

ለዓላማው ስኬታማነት ምሁራን፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሙያ ማህበራት፣ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፡ የስፖርት ቤተሰቦችና በየመስኩ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅ ለእጅ በመያያዝ ተግባራዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አሜን ኢትዮጵያ ጥሪውን ያስተላልፋል።

በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በቂ መረጃ አግኝተው እንደየአቅማቸው በሀሳብ፣ በጉልበት፣ በቁሳቁስ ወዘተ የበኩላቸውን አስተውፅኦ እንዲያበረክቱ ያሳስባል።

የአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ግቡን መትቷል የምንለው በ2000 ዓ. ም. መግቢያ ላይ የተሰፋ ተጓዦች ኢትዮጵያ ውስጥ እንደገቡ የተለያዩ የህበረተ-ሰብ ክፍሎችን ያሳተፈ ጉባኤ ከማዘጋጀት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይገደኛል የሚሉ ሁሉ ለመሰል በጎ ዓላማዎች ራሳቸውን አሰልፈው፣ በመስማማት፣ በመቀባበልና በመከባበር ለአገራችን ሰላም፣ እድገት፣ ብልጽግናና ልቆ መታየት፤ ያለማመንታት ጥረቱ ሲቀጥል ነው።

## ማጠቃለያ

ይህ የአሜን ኢትዮጵያ በጎ ራእይና የተሰፋ ንግደት ወደ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የወንድማማችነትና የመልካም ትብብር መንፈስ የምንሸጋገርበት ምዕራፍ እንዲሆንልን እንመኛለን።

ያለፈውን ታሪክ መቀየር ባንችልም ስላለፈው ታሪክ መልካም ያልሆነውን አመለካከት መቀየር እንችላለን። በቀልን ነቅሎ ይቅርታን በመትከል፤ ጥላቻን በፍቅር በመተካት፤ ካለፈው ታሪክ ጋር በመታረቅና፤ በቅንነት በማሰብ፤ ያሁኑ ጊዜ ምቹ፤ የወደፊቱ ብሩህ መሆን የሚችልበትን መንገድ ለመፈልግ ሁሉም እንደሚተባበር ተስፋ እንደርጋለን።

አሜን እውነት ማለት ነው። አሜን አበው ሲመርቁን ምርቃቱ በእውነት በእኛ ላይ አንዲፈጸም የምንሰጠው ምላሽ ሆኖ፤ መቀበልና መቀባበልን ያመለክታል።

አሜን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እርስ በርስ አሜን በመባባል አዲሱን ዘመን እንዲጀምሩ ይማጸናል።

## የአሜን ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ መዋቅራዊ ቅርፅ

መዋቅራዊ ቅርጹና አጭር የሥራ ክፍፍሉም እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ዓቢይ ኮሚቴ

ዓቢይ ኮሚቴ ተብሎ የሚታወቀው በሆላንድ ውስጥ በሚገኘው አድማስ ድርጅት ሥር የተቋቋመው በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙርያ የተነደፋትን መርሐ ግብሮች ተግባራዊ እንዲሆኑ መመርያዎችን በማውጣት እንቅስቃሴውን በበላይነት የሚያስተባብር አካል ነው።



ዓቢይ ኮሚቴው መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ የአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ እንዲስፋፋ፤ በተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ኮሚቴዎችን በማቋቋም፣ ሥራቸውን ይከታተላል፡ የሚከናወኑትን ተግባራት በበላይነት ይመራል፣ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፤ በአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ ዙርያ በስፋት እንዲሰራ ጥረት ያደርጋል።

## ኮሚቴ

ኮሚቴ የሚባለው በዓቢይ ኮሚቴው ወይም በራስ አነሳሽነት በየአገሩ የሚቋቋም ተጠሪነቱ ለዓቢይ ኮሚቴ የሆነ በተቋቋመበት አገር የአሜን ኢትዮጵያ ተጠሪ አካል ነው።

ኮሚቴው የአሜን ኢትዮጵያን ዓላማ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲሰርፅ በማድረግ፤ በየአከባቢው ንኡሳን ኮሚቴዎችን በማቋቋምና፣ በማስተባበር፡ ከዓቢይ ኮሚቴው ጋር በመመካከር፣ ከተቋቋመበት አካባቢ ጋር የሚጣጣም የሥራ ዕቅድና መመርያ አውጥቶ ይሠራል።

## ንኡስ ኮሚቴ

ንኡስ ኮሚቴዎች የሚባሉት በየአገሩ በተቋቋሙ ኮሚቴዎች ሥር ሆነው ተጠሪነታቸው ለኮሚቴው የሆኑ የየአገሩ ንኡሳን አካሎች ናቸው።
እርስዎም ይህንን የአሜን ኢትዮጵያ ዓላማ እንደሚደግፉና በስራውም እንዲሳተፉ ተስፋ በማድርግ ከዚህ በታች በተመለከተው አድራሻ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እንደሚችሉ በአክብሮት እንገልጻለን።

### ተጨማሪ መረጃ

ድረ-ገጽ www.amenethiopia.com
ኢሜል info@amenethiopia.com

ስልክ ፡ አውሮፓ
Amsterdam + 31 6 1257 6245
Brussels + 32 48686 9738
London + 44 79 5078 3292
Rome + 39 334 382 36567

ስልክ ፡ አሜሪካ
Washington DC + 1 703 231 5329
Columbus + 1 614 483 9430
Atlanta + 1 612 978 7849
California + 1 510 501 1045
Toronto + 1 416 817 1978